የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፴፫
አዲስ አበባ ግንቦት ፭ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

19th Year No. 33
ADDIS ABABA 13th May 2013

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፪፻፹፭/፪ሺ፭ ዓ.ም.
የኢትዮጵያ ንግድ ድርጅት ማቋቋሚያ
የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ............... ገፅ ፮ሺ፰፻፶፫

CONTENTS

Regulation No. 285/2013
Ethiopian Trading Enterprise Establishment
Council of Ministers Regulation ..........Page 6853

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፹፭/፪ሺ፭

## የኢትዮጵያ ንግድ ድርጅትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯ (፩)(ሀ) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ንግድ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፹፭/፪ሺ፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. መቋቋም

፩/ የኢትዮጵያ ንግድ ድርጅት (ከዚህ በኋላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ) የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሰረት ይተዳደራል፡፡

፫. ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን

የንግድ ሚኒስቴር የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

፬. ዋና መሥሪያ ቤት

የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 285/2013

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE ETHIOPIAN TRADING ENTERPRISE

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 47 (1)(a) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as the "Ethiopian Trading Enterprise Establishment Council of Ministers Regulation No. 285/2013".

2. **Establishment**

1/ The Ethiopian Trading Enterprise (hereinafter the "Enterprise") is hereby established as a public enterprise.

2/ The Enterprise shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

3. **Supervising Authority**

The Ministry of Trade shall be the supervising authority of the Enterprise.

4. **Head Office**

The Enterprise shall have its head office in Addis Ababa and may have branches elsewhere, as may be necessary.

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.box 80,001

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

፭. <u>ዓላማ</u>

ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፤

፩/ ጥራትና ደረጃቸውን የጠበቁ መሠረታዊ የሆኑ ምርቶችን በተወዳዳሪ ዋጋ በጅምላ ነጋዴዎችና በቸርቻሪዎች አማካይነት ለተጠቃሚ በማድረስ ገበያን ማረጋጋት፤

፪/ ምርቶች ኃላፊነትና ተጠያቂነት ባረጋገጠ አኳኋን በጅምላና ቸርቻሪ ነጋዴዎች ለሸማቹ ህብረተሰብ ተደራሽ ማድረግ፤

፫/ ለተጠቃሚዎች በቅርበት የሚያገለግሉ የአገሪቱን መልክአ ምድር ባገናዘበ ሁኔታ የማከማቻና የማከፋፈያ ማዕከላት እንዲኖሩት ማድረግ፤

፬/ ቀልጣፋና ውጤታማ የምርቶች ክምችትና ስርጭት እንዲሁም ግልጽና ተደራሽ የግብይት ስርዓትን በብቃት የሚያረጋግጥ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስርዓት እንዲኖረው ማድረግ፤

፭/ ጠንካራና ውጤታማ የምርቶች አቅርቦትና ማከፋፈያ የሚያረጋግጥ ዘመናዊ የማኔጅመንት ስርዓት መዘርጋት፤

፮/ በአገሪቱ በዘመናዊ አሠራር የተደገፈና ውድድር ላይ የተመሰረተ የጅምላና የችርቻሮ ንግድ ስርዓት እንዲጠናከር ከግሉ የንግድ ዘርፍ ጋር በትብብር መሥራት፤

፯/ ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ የሆኑ ሥራዎችን ማካሄድ፡፡

፮. <u>ካፒታል</u>

ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር ፩ ቢሊዮን (አንድ ቢሊዮን ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፪፻፶ ሚሊዮን (ሁለት መቶ ሃምሣ ሚሊዮን ብር) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

፯. <u>ኃላፊነት</u>

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

፰. <u>ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ</u>

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

፱. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ከሚያዝያ ፲፰ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ግንቦት ፭ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም

ኃይለማርያም ደሳለኝ
የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

5. <u>**Purposes**</u>

The purposes for which the Enterprise is established shall be:

1/ to distribute basic products with the required qualities and standards through wholesalers and retailers to consumers at competitive prices to ensure market stabilization;

2/ to ensure products are sold to consumers by wholesalers and retailers in traceable and accountability manner;

3/ to expand stores and distribution centers geographically to ensure proximity and accessibility of consumers;

4/ to implement information communication technology to ascertain efficient and effective storage and distribution of products and transparency and traceability in the trading business;

5/ to implement strong back-end supply chain management system to ensure dynamic and efficient supply and distribution of products;

6/ to play a collaborative role with the private sector in strengthening modern and competitive wholesale and retailing business practices throughout the country;

7/ to engage in any other related activity for the attainment of its purposes.

6. <u>**Capital**</u>

The authorized capital of the Enterprise shall be Birr 1,000,000,000.00 (One Billion Birr) of which Birr 250,000,000.00 (Two Hundred Fifty Million Birr) is paid up in cash and in kind.

7. <u>**Liability**</u>

The Enterprise may not be liable beyond its total assets.

8. <u>**Duration**</u>

The Enterprise is established for an indefinite duration.

9. <u>**Effective Date**</u>

This Regulation shall enter into force on the 26th day of April, 2013.

Done at Addis Ababa this 13th day of May, 2013.

HAILEMARIAM DESSALEGN

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA